የካትት 23 ቀን 2006 ዓ.ም›

# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የአድዋ ድል ቀንን ለመዘከር ከጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማሕበር የተሰጠ መግለጫ

እናት ኢትዮጵያ ለሺ ዘመናት በነጻነቱዋ ኮርታ የኖረች አገር ብትሆንም በየጊዜው ከቅርብና ከሩቅ የሚደረግባትን ትንኮሳ ለነጻነቱና ለክብሩ ቀናዒ የሆነው ሕዝቡዋ ጠላቶች የእፍረት ማቅ ተከናንበው እንዲመለሱ አድርጓል፡፡

በ1880ዎቹ አውሮፓዊያን አፍሪካን ተቀራምተው ቅኝ ግዛታቸውን ለማስፋፋት በተሸቀዳደሙበት ወቅት ጣሊያንም ድርሻዋን ለመውሰድ በመመኘት ፊቱዋን በኢትዮጵያ ላይ አነጣጥራ በ1886 ዓ. ም. ኢትዮጵያን ለመውረር ዘመናዊ ጦሩዋን አዘጋጅታ ጦርነት ብትከፍትብንም  አድዋ ላይ በብልሁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክና በቆራጡዋ ባለቤታቸው በእቴጌ ጣይቱ ብጡል መሪነት እንዲሁም ከብዙ በጥቂቱ በነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፤ በነራስ አሉላ አባነጋ፤ በነራስ ጎበና አባዳጩ፤ በነባልቻ አባነፍሶ በነራስ ሚካኤል አዝማችነት በአንድ ቀን መራራ የጦር ውሎ ድልን በመጎናጸፍ ብዙ የጠላት ጦር ከነጀኔራላቸው ሲማረኩ ሌሎች በሽሽት አምልጠዋል፡፤

ይህ ድል ለኢትዮጵያ ክብርን ያጎናጸፈ በዓለም ዙሪያ እውቅናን ያላበሳት ነበር፡፡ ከኢትዮጵያም ባሻገር በዓለም ዙሪያ ላሉ ጥቁር ሕዝቦች የብርሃን ችቦ ያቀጣጠለ ነበር፡፡ እስከዛሬም በጥቁር ሕዝቦች ዘንድ የታሪክ  አሻራውን ቀርጾ አልፉዋል፡፡

የጥንታዊት ኢጥዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ይህን ቀን በሁሉም ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ደምቆ እንዲከበር ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ በነጻነትና በአንድነት የመኖራችንን ዋስትና የሰጠ የድል ቀን ነውና፡፡

በዚህ ጦርነት ሕይወታቸውን ላጡ አካላቸውን ላጎደሉ ሁሉ ልባችንን እንዳቆሰለው እናልፋለን፡፡ ከዚህ የበለጠ መስዋዕትነት ምን ይገኛል፡፡ ይህንን ግፍ እናስታውሰው እንጂ ከጣሊያን ህዝብ ጋር የመሠረትነው መልካምና ወዳጃዊ ግንኙነት በጠነከረ መልኩ መጉዋዙ ግንኙነታችንን አስተማማኝ ከማድረጉም በላይ የዓለምን ሠላም ያጠናክረዋል ብለን እናምናለን፡፡

ዘላለማዊ ክብር ለኛ በነጻነት ለመኖር ሕይወታቸውን ላጡ ሰማዕታት አባቶችና እናቶች !

ኢትዮጵያ አንድነቱዋ ተከብሮና ተጠብቆ  ለዘላለም ትኑር !